# የቃሊቲው ደብዳቤዎች፤ቅንጅት፤ዶር/ታዬና- AFD

በየካቲት የሕዝብ ዓመጽ ፍንዳታ ጊዜ የኢትዮጵያን ሕዝብ በትልቁ ወደኋላ የጎተተው ጥያቄ የድርጅት ጥያቄ ነበር ፡፡ ሆኖም ግን በጊዜ ሕዝቡን አደራጅቶ ለሥልጣን ለማብቃት የቻለ ድርጅት ባይኖርም በፍንዳታው ወቅትና ከዚያም በሕዝብ የአመጽ እንቅስቃሴ ሂደት ሕዝቡን በማስተማርና በሕዝቡ ውስጥም በመስራት ሕዝቡን ከመሰረታዊ (Grass Root) የድርጅት ግንባታ በመጀመር እስከ ከፍተኛ ሐገራዊ ደረጃ ለማደራጀት ከፍተኛ ሙከራ እንደተደረገና ስለድርጅት አስፈላጊነትም ሕዝባችን ግንዛቤ እንዳገኘ ጥርጥር የለውም ፡፡ ይህም የድርጅት አስፈላጊነትና ጠቃሚነት ከየካቲት አብዮት ወዲህ በገሀድ ያየነው ትምህርት ነው ፡፡

የወያኔ ምንግስትም አሁን እብሪተኛና ትምክህተኛ ጸረ ዲሞክራሲያዊ መሆኑ ብቻ ሳይሆን አገራችንን ኢትዮጵያን ለመበታተንና ሕዝቦቿ ለዘመናት የማይሽር ቂም በቀል በመካከላቸው እንዲሰፍን ቀን ተሌት ብሂረሰቦችን ሃይማኖቶችንና የሃይማኖት ተወካዮችን አልፎም ከጎረቤት ሐገሮች ጋር የማያቋርጥ ግጭትና የጥላቻ መርዙን በመርጨት ላይ እንዳለ ከግንቦቱ ምርጫ በፊትም ለሕዝቡ ገሃድ ነበር ፤ ከምርጫው በኋላ የበለጠ ብዥታ ለነበራቸው ለዓለም መንግሥታት ጭምር ገሃድ ሆኗል ፡፡

ይህንንም አገር በታኝ እብሪተኛ የሽብር መንግሥት ለመጣል ሕዝቡ እንደግንቦቱ በአንድ ላይ እንዲነሳ ለመጥራትና ለመቀስቀስ አሁንም ተመልሰን የካቲት 66 የሰጠንን ትሞክሮ የግንቦቱንም ምርጫ ምክንያት በማድረግ ሕዝቡ ለወያኔ መንግሥት ያለውን ከፍተኛ ጥላቻ ያሳየበትና ሀሳቡንም የገለጸበትን መንገድ ደግመን ደጋግመን ብናገላብጠው ያን ጊዜም አሁንም ነገም ሕዝብ ውጤት ያለው ለውጥ ለማምጣት ጩኸቱን የሚያሰማው ፣ ሀሳቡን የሚገልጸው ፣ ትግሉን እሙን የሚያደርገው ድርጅት ሲኖረውና ይህም ድርጅት በግልጽነትና በቆራጥነት የሕዝብ አካል ሕዝባዊ ድርጅት ሲሆን ነው ፡፡
በዚህች ትንሽ ወረቀት ላይ ሰለወያኔ እኩይነት ከማንሳት በመለስ ስለሕዝባችንና ከኛ ስለሚጠበቀው ድርጅታዊ ሀላፊነትና ብቃት ግልጽነትና ቆራጥነት ብናወጋ ተገቢ ይመስለናል ፡፡

የኢትዮጵያ ባንድነት የመኖር ያለመኖር ጥያቄ ተነስቶበት አያውቅም ፣ ግፈኛውና ፋሽስቱ የመሶሎኒ መንግሥት ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅት አገሪቱን ለመከፋፈልና እርስ በርሱ ለማማታት ብሎም የራሱ ወዳጅና ጠላት በውስጣችን ለመፍጠር ሞክሯል ፡፡ ክብሩ ይስፋ ለእግዚአብሄር አባቶቻችን ያን ደባ አውቀው በመታገል አንድነታችንን ጠብቀው አስረክበውናል ፡፡ ወያኔም ያንን (Master Plan) የሚከተል ይመስላል ፡፡ ስለሆነም ኢትዮጵያን ለመበተን ይዞት ያለውን ሴራ ግንቦት 97 የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደማይቀበለው ያለማወላወል በድምጽ አጋልጧል ፡፡ ሌሎችንም የዴሞክራሲ የፍትህ ርትእ የኢኮኖሚ ወዘተ... ጥያቄዎችን በሚመለከት ይህ የወያኔ መንግሥት መፍትሄ የማምጣት ችሎታም እንደሌለውና የሞራል ብቃት ያጣ መንግሥት እንደሆነ በተሰለፉት የተቃዋሚ ድርጅቶች ታዛ በመሆን ለወያኔ ያላቸውን ጥላቻና በይበልጥም ለቅንጅት እንዲሁም ለሕብረት ያላቸውን ድጋፍ ግልጽ አድርገው አስቀምጠዋል ይህም ኢትዮጵያዊነታቸውን በማስረገጥ ነው ፡፡

በግንቦቱ ምርጫ የቅንጅት ፓርቲ ከማንኛውም የተቃዋሚ ድርጅት የበለጠ የድምጽ ድጋፍ ያገኘ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዙ ተስፋ የጣለበት ድርጅት ነበር ፡፡ ሆኖም በርግጥም አምባገነን በውነትም ጸረ ዲሞክራሲ የምንለው ይህ የሽብር መንግሥት ለሰላም ለአንድነትና ለፍትህ የቆመ መንግስት አይደለምና የቅንጅትን የበላይ አመራር ሙሉ በሙሉ አሥር ቤት በማጎር የሕዝቡን ድምጽ ቀፍድዶ በማሰር አሁንም አገራችን ከችግር ማጥ እንዳትወጣ ሲያደርግ እኛም ለትግሉ ተገቢውን መፍትሄ ለማግኘት የሚያስችለንን መሣሪያ የድርጅትን ጥያቄ ስናፈርስና ስንሰራ እንገኛለን ፡፡

በምርጫው ላይ የተሳተፉ ድርጅቶች በሕዝቡ ውስጥ በቂ የማደራጀት ሥራ እንዳልሰሩና የተጠናከረ መዋቅር እንዳልነበራቸው እራሳቸው ድርጅቶቹ ማለት የቅንጅትና ሕብረት በይፋ የሚናገሩትና የሚያምኑት ሃቅ ነው ፡፡ ስለሆነም ነው የቅንጅት አመራር ወደፋሽስቱ ወያኔ እስር ቤት ከወረዱ በኋላ ትርጉም ያለው አመራር በህቡእ ሆነ በግልጽ በሐገር ውስጥም ሆነ በአካባቢው ሆኖ ለጊዜውም እንኳን ቀጣይነት ያለው አመራር መስጠት ያልተቻለው ፡፡ ድርጅቶቹ ለዚህ ሁኔታ የተዘጋጁ አልነበሩምና የአደረጃጀት ይዘታቸውን ይጠቁማል ፡፡

የቅንጅት አመራር እሥር ቤት ከወረደ በኋላና የደጋፊውን ሕዝብ እንቅስቃሴ ለማስቀጠልና ፈርጅ ለማስያዝ ዘላቂ መፍትሄ ለመስጠት የመሪዎቹ ከእስር ቤት መለቀቅ አይነተኛው መፍትሄ ነው

ይህ ባልሆነበት ሰዓት የሕዝቡና የመሪዎቹ ድምጽ በካቴና ተቀፍድዶ በብረት በር በተቸነከረበት በአሁኑ ሰዓት እነርሱን (አመራሩን) እንወክላለን በሚልና ቃሊቲ ያለው አመራር ሙሉ ኀላፊነት ሰጥቶን የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል ከውጭ ሐገር ሆነን እንድንመራ አስረክቦናል በሚል የቅንጅት አመራር በስደት ላይ ተግዟል ይሉናል ፡፡

ይህ አቀራረብና አመጣጥ ከጽንሰ ሀሳቡ እስከ ግብሩ ከመጀመሪያውም በአባላቱና በደጋፊዎቹ መካከል ትልቅ ተቃውሞና ጥያቄ ያስነሳ ከመሆኑም በላይ ብዙ የቅንጅት አባላት ከትግሉ ገሸሽ እንዲሉ የቀሩትም ተከፍለው አንዱ ሌላኛውን በማውገዝና በመኮነን ሥም በማጥፋትና በማራከስ ተግባር ተሰማርተው እንደቆዩ ገሃድ ነው ፡፡ ይህ በሚካሄድበት ወቅት የቅንጅትን አንድነትና ውህደት አለመጠን ጎድቶታል ፣ በጠቅላላው የሕዝቡን እንቅስቃሴ ግለት አብርዷል ፣ ሕዝብ የመረጣቸው መሪዎች ላይ ያላግባብ ትችቶችና ጥያቄዎችን አስነስቷል ፣ በሌሎች ኢትዮጵያውያን ድርጅቶች የማደራጀትና የማታገል እንቅፋቶችን ፈጥሯል ፡፡

ይህ ከቃሊቲ ሙሉ ውክልና አግኝቻለሁ የሚለው ቡድን የኢትዮጵያን ህልውና ከሚፈታተኑ ድርጅቶች ጋር በፈጠረው ሽርክና (AFD) በውስጥም በውጪም ያስነሳው ተቃውሞ እንዲህ ዓይነት ተግባርና ድርድር ውስጥ ለመግባት ሀላፊነትና የፖለቲካውም ብቃት (Skill) እንደሌለው ግልጽ ነበር፡፡

ከዚህም ችግር በኋላ በመካከሉ በተፈጠረው በገንዘብ ሳቢያ የመጣው ችግር ከገንዘብ ጥያቀ በላይ ሄዶ የአሰራር የአመለካከትና ከሁሉም በላይ የቅንጅትን የውህደትና የአንድነት ጥልቀቱን እያመላከተ ነው፡፡ይህ ችግር በቶሎ ለመፈታት አለመቻሉ በየጊዜው የሚነሱትን ወቅታዊ ጥያቄዎች በቅጡ እንዳይታዩ አርጓቸዋል፡፡ወያኔም በድርጅቱ ውስጥ ሠርጎ እንዲገባ (ከመጀመሪያውም አብሮ ተመስርቶ ካልሆነ) በሩን ወለል አርጎ ከፍቶለታል፡፡ቅራኔዎቹ እንዲሰፉም አመቺ የፕሮፐጋንዳ ነጥቦች እየመገቡት ነው፡፡

እነዚህ ተወክለናል የሚሉ አሁን በሁለት ወገን ተሰልፈው “እኔ ነኝ ተወካይ” አንተ አይደለህም በሚል እርስ በርሳቸው ሲናኮሩና ለሐገርም ብሎም ለሕዝብም ትግል ላይ ጉዳት ከማድረሳቸውም በላይ አሳዛኝና ማፈሪያ ተግባራቸውን እንደ ፖለቲካ ስልት ይዘውታል፡፡

በውጭ ሐገር ያለው ኢትዮጵያዊ እነዚህን ሰዎች ለመምከርም ገንቢ ነቀፌታም ለማቅረብ ወደኋላ ያለበት ጊዜ የለም፡፡አገር ቤት ያለው ሕዝብ በሁኔታው ማዘኑ ብቻ ሳይሆን በቅንጅት ላይ ደባ እንደሚሠራ በተለያዩ መንገድ እንደሚገልፀው ድብቅ አልሆነም፡፡”<u>የታሰሩት ይፈቱ”</u> ብሎ በተቀናበረና በተደራጀ መልክ አንድ ወጥ እርምጃ መውሰድ ከሚጠበቅብን በጣም አነስተኛው ተግባር ነበር፡፡ነገር ግን በነዚህ “የውጭ ተወካዮች” ነን ባዮች ምክንያት ብቻ በጠቅላላው የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ ለማለት ቀርቶ የቅንጅት መሪዎች ይፈቱ ብሎ በነጠላ ለመጮህ እንኳን ያልተቻለበት ሁኔታ ተደርሷል፡ማፈሪያ የምንለውም በንዴትና ከትእግስት በላይ ስለሆነ ነው፡፡በራሳቸው ላይ ያለውን በሽታ ለማየት ሲያቅታቸውና ሲሸፋፍኑ ሁለቱም ወገኖች ይህን ችግር የፈጠረብን ወያኔ በውስጣችን ገብቶአል ይላሉ፡፡ይህን ካወቁ እራሳቸውን ከዚያ ማጥራት ነው፡፡ሌላ መፍትሄ የለውም፡፡ኢሕአፓ ነው ይሉናል፡፡ ኢሕአፓ በቅንጅት መጠናከር ይጠቀማል እንጂ ይጎዳል ብለን አናምንም፡፡ኢሕአፓ እኛ ማየት ካቃተን በላይ ጠንካራ ሆኖ በነሱ ውስጥ ገብቶ የሚበጠብጣችው መሆኑን ካወቁ ኢሕአፓ ናቸው የሚሏቸውን መንጥሮ ማስወጣትና መቀጠል ነው፡፡የናቴ መቀነት አደናቀፈኝ ሕዝባዊ ትግል ውስጥ ቦታ የለውም፡፡

ዋናው ምክንያት ግን በውስጣቸው የጠራና የሰከነ ውህደት ባለመኖሩ አሁንም ድሮ ይዘውት የመጡትን የየግል ድርጅት ታማኝነታቸውን ባህሪ አውልቀው ወደ ቅንጅት ድርጅታዊ እምነትና ባህሪ ስላልቀየሩት ወይም ስላልተቀየሩና ቅንጅትን እንደ አንድ የተዋሃደ አንድ ወጥ ፓርቲ ሳይሆን እንደ ግንባር ይዘውት ስለሚጓዙና ሌላው ደግሞ በእምነት በጥራትና ብስለት የአመራር ችሎታ ሳይሆን በግል መተዋወቅ የተጠራቀሙ በመሆናቸው ይህም በመሰረቱ ይዞት የመጣው የፊውዳል ኢንትሪግ (Feudal Intrigue) የአሰራሩ መሰረታዊ ባህሪ በመሆኑ በእለት ተእለት ሥራቸውና የሀሳብ ልዩነት አያያዛቸው ሲንጸባረቅ ይታያል፡፡

ይህ መሰረታዊ ድርጅታዊ አወቃቀርና አሠራር ለውሸትና፡ለክህደት፡ለተንኮል፡የተጋለጠ ስለሆነ እነርሱም በዚህ የተካኑ በመሆናቸው ሁል ጊዜም አንዱ ሌላውን እንዴት ብልጥ ሆኖ እንደሚያጠቃው እንጂ እንዴት ሀቀኛ ሆኖ ለትግሉም፡ለታሰሩትም መፈታት አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ሲሰራ አይታይም፡፡ይህ ባህሪ (Inherent) ስለሆነ በቶሎ ሊታረም አይችልም ይቀጥላል፡፡

እነዚህ ቅንጅት ወክሎናል የሚሉ ሁለት ቡድኖች በየጊዜው ዋና መረጃ አርገውና ለሥልጣን መነሻ የሚያረጉት ዶኩመንት ከቃሊቲ እስር ቤት በአብዛኛው “<u>ከኢንጂኒየር ኃይሉ ሻውል ተላከ”</u> የሚባል ቁጥር ስፍር የሌለው ደብዳቤ ነው፡፡ከ (AFD) መፈጠር እስከ (KIL)ና ቅንጅት (KNA) መወለድና መገመስ አሁንም ደግሞ የአስታራቂ ቡድን ከሐገር ቤት መምጣትና እንደገና <u>“ጋብቻ ለአንድ ሳምንት ብቻ ፡ ተመልሶ ጠብና ሽኩቻ”</u> የሆነበት ዛሬም እንደትላንትና በቃሊቲ እሥር ቤት በሚማቅቁት መሪዎች ሥም በአሉባልታ ደብዳቤ በቅንጅት ፓርቲ ሥም ሥልጣን ሲነገድ እናያለን፡፡ይህ ችግር አሁንም ሌላ (Council) የሚባል ወልዷል፡፡

ይህን ያህል ደብዳቤ የሚገባና የሚወጣ ከሆነ ፡ በቃልም ሆነ በጽሑፍ እንደዚህ በቀላሉ የሚንሸራሸር ከሆነ አመራር  ከእስር ቤት ሆኖ የማይሰጥበት ምክንያት አይታየንም፡፡

ይህ እንዲህ እንዳለ ችግሩ በጣም ተፋፍሞ በቃሊቲ እስር ቤት ያሉት የጥፋተኛ ፍርድ ተፈርዶባቸው የመጨረሻ እድላቸውም ምን ይሆን እያልን በምንጨነቅበት ወቅትና የቅንጅት አስታራቂ መልእክተኞች ከቃሊቲ አመጣን ከሚሉት ደብዳቤ አንዱ የዶክተር ታዬ ወ/ሠማያትን እና የአቶ ክፍሌ ሙላትን ሥም ያዘለ እንደነበረ ይታወሳል፡፡ በዚህ መጣ በሚባለው መልእክት አማካይነት አቶ ክፍሌ ሙላት አሁንም እንደ ጋዜጠኛና እንደ ማሕበራቸው መሪ ሆነው መቀጠሉን ሲመርጡ፡ ዶክተር ታዬ ግን "የቃሊቲ አመራሮች እስከጠየቁኝ ድረስ ያሉትን በደስታ እፈጽማለሁ፡ህይወቴንም ቢሆን እሠጣለሁ" ብለው በመቀበል የቅንጅት ሰሜን አሜሪካውን ቡድን (የነሻለቃ ዮሴፍ ቡድን በመባል የሚታወቀውን) በመቀላቀል በሊ/መንበርነት የአመራሩን ሥልጣን ተረክበው የድርጅታቸውንም ሥም በመቀየር (KIC) የቅንጅት ኢንተርናሽናል ምክር ቤት(Council) ብለው ከቀጠሉ ትንሽ ቀናትን አሳልፏል፡፡

በርሳቸው ወደ አንደኛው ክፍል መቀላቀል ሌላኛውን ክፍል (KIL)ን በጣም እንዳስቆጣውና የ(KIL) አመራሮችም በአደባባይ ውግዘታቸውን እንዳሰሙ አይተናል፡ ዶክተር ታዬ ባሉበት ሐገር ውስጥ በእሳቸው ላይ ምንም ዓይነት የማስፈራራት ጫና ሳይደርስባቸው በራሳቸው ህሊና ግራና ቀኙን ተመልክተው ለማደርገው ትግልና አስተዋጽዖ ለኔም ለሐገሬም ይጠቅማል ብለው በራሳቸው ተነሳስተው ያደረጉት ውሳኔ ነው፡ ብለን እናምናለንና በዚህ ውሳኔያቸው በመረጡት ድርጅት መግባታቸው የራሳቸው ምርጫ ስለሆነ አንዳችም የመቃወም መብት ያለን አይመስለንም፡፡የገቡበት መንገድ ወዘተ…የሚባለው የቅንጅቶች ችግር ነው፡፡ በርግጥ ዶክተር ታዬ በኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ውስጥ የቆዩ የበሰሉና ለአጠቃላይ ለሕዝብ አንድነትና ነፃነት ሲሉ ከወያኔ ጋር ግብ ግብ የገጠሙ በወያኔ እስር ቤት ለረጅም ጊዜ የማቀቁ፡ ችግርና መከራ ሳይበግራቸው ለወያኔ ሳያጎበድዱ በኢትዮጵያ፡ በህዝብና በዓለም አቀፉ የተለያየ ሰባአዊ ፍትህ ጩኸቶች ጫና ህይወታቸው የተረፈ ታጋይ መምህር እንደሆኑ አንዘነጋም፡፡ አሁንም ቅንጅትን ተቀላቅያለሁ እስካሉበት ድረስ ለኢትዮጵያ አንድነትና ነፃነት ውህደት ትግል ከወያኔ ጋር ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያዊነታቸውን ከካዱ ከኢትዮጵያም ለመገንጠል ቀን ተሌት ከሚሰሩና ከሚያሴሩ ድርጅቶችም ሆነ ሐገሮች ያለማቋረጥ ሲታገሉ እንደነበር የማይካድ ሀቅ ነው፡፡

ዶክተር ታዬ ወ/ሠማያት ከቃሊቲ በተጠየኩት መሰረት አረጋግጬ እቀበላለሁ ወይም አልቀበልም ብለውን ነበር፡፡ በዚያም መሰረት አሁን ቅንጅት ውስጥ ይህን ኃላፊነት በመያዝ ሲገቡ <u>ከቃሊቲ አረጋግጠው</u> ነው ብለን እንገምታለን፡፡

ይህም ማለት ደግሞ ቃሊቲ ያሉ መሪዎች የነሻለቃ ዮሴፍን ቡድን እንዲቀላቀሉና እንዲያጠናክሩ በተጨማሪ መመሪያ ሠጥተዋል ብንል (በኛ ትርጉም) ስህተት አይሆንም፡፡ ይህ (Logic) ትክክል ከሆነ (KIL) በቃሊቲ ተቀባይነት የለውም፡ የነዶክተር ታዬን ወገን (KIC)ን መቀላቀል ወይም መፍረስ አለባቸው ተብሏል ወደሚል ድምዳሜ ይወስደናል፡፡ አለበለዚያ እንደ (Faction) ወይም (Renegades) ሆነው የቀጥላሉ ማለት ነው፡፡ እውነትም የሚያስመስለው (የሃሳቡን ተዋረድ (Logic)ን ማለታችን) የ(KIL) ሁለት አባላት ተገንጥለው ምክር ቤቱን (Council)ን መቀላቀላቸው ነው፡፡

አሁን ውጭ ባለው ኢትዮጵያዊ መካከል ሰፊ ክርክርና መከፋፈልን መካረርን ያስነሳው የእንቶ ፈንቶው ቅጥ ያሳጣው በምእራቡ ዓለም ተጽፎ የኢትዮጵያ ቴምብር እየተለጠፈበት ወደ አሜሪካ ተመልሶ እየመጣ የሚነበብልን ደብዳቤ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የዶክተር ታዬ ወ/ሠማያት አቋምና በዚህ ቅጥፈትና ውሸት በተሞላበት ዝብርቅርቁ በወጣ ቦታ ገብተው ችግሩ ሲከር ማየታችን ነው፡፡

ዶክተር ታዬን እንደመሪ እንጂ እንደተራ ግለሰብ የማናያቸው ግለሰብ መሆናቸውን ግልጽ ነው፡፡ ስለሆነም ነው በመሪነት ደረጃ ከፍተኛ ሚና የተጫወቱና የሚጫወቱን ኢትዮጵያውያን በሚያደርጉትና በሚሰሩት ሁሉ በአንክሮ እያየን የምንከተላቸው፡፡ እርሳቸውም እንደ (Civic Organization) መሪነታቸው ባለፉት ወራቶች የተቃዋሚ ድርጅቶችን የ(Civic) ማሕበራትን የታወቁ ግለሰቦችን ለማሰባሰብ የሚያደርጉት ጥረትና ውጤት ፍሬውን ለመስማት በጉጉት እንጠብቅ የነበረው፡፡ ይሁንና ይህ ጥረት ውጤት አመጣም አላመጣም ከአሁን በኋላ የርሳቸው ሚና በፖለቲካ ድርጅት ውስጥ ለመጫወትና አስተዋጽዖ ለማድረግ በወሰኑበት ሁኔታ ተቃዋሚዎች የሚያነሷቸውን አንዳንድ ነጥቦች ጠቁመን በመሰለን ደረጃ አለአግባብ መሆናቸውን አሳይተን ወደራሳችን ነጥብ እንመለሳለን፡፡

- ዶክተር ታዬ የቅንጅትን ማኒፌስቶ አልቀበልም ያሉ ሰው ናቸው፡፡
- ዶክተር ታዬ ድሮ ኢሕአፓ የነበሩ አሁንም ኢሕአፓን የሚደግፉ ሕብረቱን የሚደግፉ ናቸው/ነበሩ
- ዶክተር ታዬ (KIL)ን ሆነ (KNA)ን ሲያወግዙ የነበሩ ናቸው
- ዶክተር ታዬ (AFD)ን ማውገዝ ብቻ አይደለም የምንዋጋው የኢትዮጵያ ጠላቶችና የኢትዮጵያን አንድነት የሚፃረሩ ጥርቅምቅሞች ናቸው (ከቅንጅት በስተቀር) የሚሉ የነበሩ ግለሰብ ሲሆኑ አሁን ሥልጣን ስለተሰጣቸው ነው የሚሉም አሉ፡፡

ከ(AFD) በስተቀር በቀረው አንስማማም አሁንም ቢሆን አንድ ሰው ሙሉ በሙሉ 100% የማንንም ድርጅት ፕሮግራም ሳይቀበል አብዛኛውን በመቀበል ብቻ አባል መሆን ይችላል፡ የአንድ ድርጅት (Core, Pillar) የሚባሉ መሠረታዊ የሆኑ ነጥቦች ድርጅቱ የማይደራደርባቸው የእምነቱ መግለጫና ከሌላው ድርጅት የሚለየው የፕሮግራሙ ነጥቦች ይኖራሉ፡ ነገር ግን መላው አባላት ከላይ እስከታች ብዙሀኑ ያመነበትን ተቀብለው ይሄዳሉ በሥራ ይተረጎማሉ፡ ይህን ከአመራሩ ጀምሮ ነጥብ በነጥብ ይስማማበታል ማለት አይደለም፡፡ ለብዙሀን ይገዛሉ፡፡

ይህን ካልን በኋላ ዶክተር ታዬ አሁንም ልዩነታቸውን ይዘው ገብተው ሊሆን ይችላል፡ ተቀባይነት አለ ማለት ነው ወይም አቋማቸውን ቀይረዋል ማለት ነው፡፡ ነውርም አይደለም፡፡

ኢሕአፓ ነበሩ የሕብረት ደጋፊ ኛቸው/ነብሩ፡ የሚለውም ዶክተር ታዬ የኢሕአፓ አባል ወይም የሕብረት አባል ለመሆናቸውም ምንም ማስረጃ የለንም፡፡ ነገር ግን የኢሕአፓ ወይም የሕብረት አባል ቢሆኑ ኖሮ እንኳን በቆራጥነትና በወያኔ ተቃዋሚነት መታገላቸውን ለሐገር አንድነት የሰሩና የከፈሉ በመስራትም ላይ ባሉ ድርጅቶች ውስጥ የሚያኮራና (Constantly) አሁንም የበለጠ አስተዋጽዖ አደርጋለሁ ወደሚሉት ድርጅት ማዘንበላቸውን በፀጋ ልንቀበላቸውና ልንኮራበት እንጂ ልናፍርበት ወይም የወቀሳ የዘላፋ ምክንያት አይደለም፡፡የሚያሳፍረውና የሚያስወቅሰው ኢትዮጵያን ሲረግጥና ሲጨፈጭፍ በነበረው የፋሽስቱ ደርግ ሊቀመኳስ የነበሩ፣ ደርግ ሲወድቅ ደግሞ የጸረ ኢትዮጵያው ወያኔ አፈንጉስና ጸሐፊ ተዛዝ ሆነው ሲሰሩ የነበሩ አሁንም ከዚያው ያልተላቀቁ በቅንጅት ውስጥ ተሰግስገው ቅንጅትን በደጀዝማችና በቢትወደድነት ማእረግ የሚመራ የአስቸኳይ ጊዜ የአርበኞች ማሕበር አስመስለው የያዙትን የቅንጅት ቁራጥ አባል ነን የሚሉትን እየጠቀሱ መውቀስና መተቸት በተገባ ነበር፡፡ አሁንም ከያዛቸው አባዜ እንዲላቀቁ ማረግ ነው፡፡

ዶክተር ታዬ (KIL)ን ሆነ (KNA) ያወግዙ ነበር ለሚለው ከላይ በሰጠናቸው ማመሣከሪያዎች ሚዛን ማየት ይቻላል፡፡ በደረሱበት ጥናት ወይም ደብዳቤ በሚባለው ታምረኛ ወረቀት (KNA)ን ተቀብለው ገብተዋል የ(KIL)ን ቀሪ አመራር አባሎች በግለሰብ ለመመለስ እያባበሉ ነው፡፡ በኛ በኩል ምንጊዜም የተጠናከሩና የተደራጁ ባይሆኑም ኢትዮጵያዊነታቸውን በማንጠራጠራቸው ለኢትዮጵያ አንድነት ዋና ተግባር አርገው በሚታገሉ ድርጅቶች መካከል የሚነሳ ችግርና ልዩነት እርስ በራሳቸው ወይም በሐገር ሽማግሌ ወይም ያለው የሐገር ቤት የፖለቲካ ሁኔታ ሲሰማቸው በአንድነት ተቀራርበው ይሰራሉ ብለን እናምናለን፡ አሁን ያለው መከራከርና መነናተል የሚበርድበት ጊዜ ይመጣል ብለን ተስፋ እናደርጋለን፡፡

## ዶክተር ታዬና (AFD)

ቅንጅት (የውጭ ሐገሩ) በሻቢያ ከበሮ እየተደለቀ የተፈረመውን (AFD) ለኢትዮጵያ ትግል የማይጠቅም አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያን ለማፍረስ የአንድነት ኃይሎችን ለመበታተንና ለማዳከም ኢትዮጵያን ለማጥፋት የተነሱ ኃይሎች ድጋፍ አርጎ ኢትዮጵያን ለመገነጣጠል በዴሞክራሲ ሥም ኢትዮጵያዊነታቸውን ከደው የኢትዮጵያን ህልውና የሰረዙ ኃይሎች ጋር ኢትዮጵያዊው ድርጅት ቅንጅት ከነዚህ ፀረዎች ጋር በመሰለፉ ከፅንፍ እስከ አፅናፍ መላው ኢትዮጵያዊ እንደተቃወመውና የዚህም ተቃውሞ አስፈላጊ እንደሆነ ዶክተር ታዬ በተለያየ መድረክ ሲያስረዱና ሲያስተምሩ ቆይተው ነበር፡፡

ከቅንጅት በስተቀር (OLF እና ONLF) አሁንም (AFD)ን በምስክር ወረቀትነት ከመጠቀም ሌላ በኢትዮጵያ ውስጥ በሕዝባችን እያደረሱ ያለውን ጉዳት ዓለም እያየው ባለበት ወቅት (KIL)ና (KNA) ጆሮ ዳባ ልበል ብለው ግትር በመሆን ከማሕበሩ በመውጣት ኢትዮጵያውያንን ከማሰባሰብ ይልቅ የ(OLF) ታማኝ ሆነው ተቀምጠዋል፡፡

AFD ከተመሰረተ በኋላ በወረቀትም ሆነ በጠመንጃ (OLF)ና (ONLF) ማንነታቸውንና ከአላማቸውን ፍንክች እንዳላሉ ዛሬም ይህን ጽሑፍ ስናዘጋጅ ዶክተር ታዬም ሊቀመንበርና ሥራ አስኪያጅ በሆኑበት የቅንጅት (Council) ውስጥ 2ኛው መግለጫ ላይ የመጨረሻው ነጥብ <u>(AFD) ማጠናከር</u> ዋናው ተግባር መሆን እንዳለበት ማረጋገጣቸው ሳያሳስበን አልቀረም፡፡ ቢያንስ ይህ ጥያቄ ቅንጅትን እንዳዳከመውና በአገር ውስጥም በውጭ ሐገር ያለውን እውነተኛውን ኢትዮጵያዊ እንደበታተነውና እንዳዳከመው በጣም ግልጽ ሆኖ ሳለ አሁን በአዲስ ኃይል የተዋቀረው (Council) ቢያንስ በቆይታ ተይዞ እንደገና ቢጠናና የተሻለ ሁላችንንም የሚያሰባስብ መንገድ መፈለግ ተገቢ በሆነ ነበር፡፡ እኛ ተዳክመን (OLF) ማጠናከር በኢትዮጵያ አንድነት ላይ መፈታተን መሆኑን ድሮ ያዩበት በነበረው አመለካከት ማየት ተገቢ ነው እንላለን፡፡ ይህ የቅንጅት አባላት ጥያቄ ብቻ ሳይሆን የሁሉም ኢትዮጵያዊ ጥያቄ መሆኑን ከወዲሁ ማየት የወደፊቱን ችግርና ልዩነት ያጠበዋል እንላለን፡፡ አለበለዚያ ከቃሊቲ ደብዳቤ መጣ ሄደ ማለት ያረጀ ያፈጀ ምክንያት ነውና ዶክተር ታዬ ይህንን ጥያቄ ገና

ከመግባትዎ ተቀብለው ለማጠናከር መጀመርዎ በጣም አሳስቦናል፡፡ ለወደፊትም ለሚኖረን ድጋፍና አንድነት የነበረውን ችግር ያጠናክረዋል እንጂ አይፈታውም፡፡

AFD የቅንጅት ችግር ብቻ አይደለም፡፡ (AFD) የመላው ኢትዮጵያውያን የአንድነት ኃይሎች ሁሉ ችግር ነው፡፡የቅንጅት ወኪል ነን ባዮች በዚህ ትብብር ውስጥ ገብተው በመፈረማቸው ለኢትዮጵያ አንድነትና ለቅንጅትም ህልውና ይታገሉ የነበሩ ግለሰቦች ራሳቸውን ከቅንጅት ያራቁበትና አንዳንዶችም ከትግሉ ጨርሰው የራቁት በዚህ ምክንያት መሆኑ ግሃድ ነው፡፡ እነ አምባሳደር እምሩ፡ እነ ኮማንደር አሰፋ ሰይፉ፡ እነ ኮሎኔል አስናቀ (በትንሹ ለምጥቀስ) የመሰሉ ታላቅ የሐገራችን የፖለቲካ አዛውንቶች የ(AFD)ን ምሥረታ አጥብቀው ሲቃወሙ ከስልጣን ፍላጎት ወይም ቅንጅትን ለመበተን ወዘተ...ሳይሆን የኢትዮጵያን አንድነት ለሚፃረሩ ድርጅት ነን ባዮች ቅንጅት ለነዚህ ቡድኖች ከጭቃ ላይ አንስቶ ለሐገራችን መበተን ሕጋዊ መድረክ እንዲያገኙ በመጋበዝ ፡ ተባባሪ ስለሆነ ነው፡፡

ይህ ጥያቄ የአንድ ወይም የሁለት ኢትዮጵያዊ ፖለቲካ ድርጅቶች ጥያቄ አይደለም፡፡ ማንኛውም ነገር በኢትዮጵያ አንድነትና ህልውና ላይ ሲመጣ የሁሉም ድርጅቶች ሆነ ግለሰቦች ዋና ጉዳይ ይሆናል፡፡

ማንም ኢትዮጵያዊ ድርጅት የኢትዮጵያን አንድነትና ብልፅግና አመጣሁ ብሎ ሲነሳ አይዞህ በርታ አብረንህ ቆመናል እንደምንለው ሁሉ፡ ኢትዮጵያን ወይም "የኢትዮጵያን ትግል ይጠቅማል" በሚል የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነት የሚጎዳ እርምጃ ሲወስድ ተቃውሟችን የጠነከረ ይሆናል፡፡

ቅንጅት በምርጫው አሸነፈ ማለት የኢትዮጵያን የወደፊት እድል እንደፈለገው ለማድረግ ነፃ መንገድ ተከፍቶለታል ማለት አይደለም፡፡

ድርጅቶች የሕዝብ ድጋፍ አለን በሚል ትምክህትና ትእቢት ሊያዳብሩ እንደሚችሉ የምናውቀው ሃቅ ነው ይህ በ(KIL) መሪዎች ቅንጅት (Mandate) አለው ሲሉን ከርመዋል የኢትዮጵያን አንድነት ለመገንባት እንጂ ኢትዮጵያን ጥያቄ ውስጥ ለማስገባት ማንም (Mandate) የለውም ዶክተር ታዬም ቅንጅት ውስጥ መግባታቸው ችግሩን መስመር ለማስያዝ ይረዳ ይሆናል የሚል ተስፋ ነበር ያለን፡፡ ነገር ግን አሁን የዶክተር ታዬ አቋም (Council)ን ጨምሮ (AFD)ን ለማጠናከር ተግተው መሥራት ያለባቸውና ከተቀዳሚ ተግባሮቻቸው አንዱ ለመሆኑ በሁለተኛ ጋዜጣዊ መግለጫቸው ሰኔ 17/99 አስቀምጠውታል፡፡አጠናክሮ ለመስራት ወይም የተጠናከረ እርምጃ ማለት ምንድነው ብለን ብንጠይቅ

1. ከ(OLF) ጋር ትሥሥር ማጠናከር፡ የተጣመረ እርምጃ በጋራ መስራት ነው፡ ይጠበቃል፡፡
2. ከሻቢያም ጋር ወደድንም ጠላንም የግድ ግንኙነት መቀጠል ሳይሆን ትእዛዛችን ጭምር መቀበል የነሱን ጥቅም ማስከበር የግድ ነው፡፡
3. እኛ ከዚህ ጥያቄ ላይ (እኛ ስንል ዶክተር ታዬን ጭምር) ባለፈው አንድ ዓመት የ(AFD) ጉዳት በዝርዝር ማስረዳት ኢትዮጵያን ፖለቲካ ሁኔታ ጥሩና አጥጋቢ ግንዛቤ እንድናገኝ ተደርጎ ጥያቄው ወደ ግባአተ መሬቱ ከተላከ በኋላ ዶክተር ታዬ በአዲስ መልክ ይህን ጥያቄ ሲያነሱ የሞተውን በሽታ መቀስቀስ ከመሆኑም በላይ በመካከላችን ያለው የፖለቲካ ግንኙነት መጥፎ አቅጣጫ ሊይዝ እንደሚችል ካሁኑ ግልጽ መሆን አለበት፡፡

እኛ ከ(OLF) ጋር ሆነ ከ(ONLF) ወዘተ...ጋር ችግር ሊኖረን አይገባም ነበር ፡ በዲሞክራሲ ጥያቄ ሥም የኢትዮጵያን አንድነት እስከተቆራቆሱና እስከተፈታተኑ ድረስ አብሮ መስራት የሚለው ከጥያቄ ውጪ ነው፡፡ኢትዮጵያ ብሎ መጥራት ወይም ኢትዮጵያዊ ተብሎ መሰየም የማይፈልግ ቡድን ከኢትዮጵያዊ ቡድን ጋር ጉዳይ የለውም፡፡ አጥፌና ጠፊ አብረው ስለማይሄዱ አሁንም (AFD) በዶክተር ታዬ ተነሳ ወይም በሌላ ተዳሰሰ (OLF)ና መሰሎቹ በግልጽ ጥያቄያቸው በኢትዮጵያዊነትና በኢትዮጵያ ውስጥ እንደማንኛውም የዲሚክራሲያዊ ጥያቄ እንጂ የኢትዮጵያን አንድነትና ህልውና የሚፈታተንና ወደ ጥፋት የሚያመራ እስከሆነ ድረስ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ድርጅት አብሮ ላለመስራት እንጂ አብሮ ለመስራት የሚፈራረምበት ሁኔታ ሊኖር አይችልም፡፡(OLF)ን ሆነ ሌሎችን የምንቀርበውና አብረን የምንሰራው በአንድ ሁኔታ ብቻ ነው፡፡ ይህም የሚመሩበት የፖለቲካ ፕሮግራም ወርውረው ኢትዮጵያዊነታቸውን በማያወላውል ሁኔታ ሲያስረግጡና ሲቀበሉ ከዚያም ጥያቄያቸው የኢትዮጵያን አንድነት አስረግጦ በኢትዮጵያ ውስጥ መፍትሄ ሊሰጠው የሚገባና የሚችል የዲሚክራሲ ጥያቄ ለመሆኑ ይህንንም የሚያንጸባርቅ ፕሮግራም ነድፈው በአዲስ መንፈስ ሲቀርቡን ብቻ ነው፡፡ ይህ ነጥብ የምናጠናው የምንዘክረው እነርሱም ወዲህና ወዲያ ሊያወላውሉበት የሚገባ ጥያቄ አይደለም፡፡ ወንድምነታቸውን አውቀን የአንድ ሐገር ሰዎች እንደሆንን የማንከራከርበት ነጥብ በመሆኑ ሁልጊዜ አብረን እንደ ኢትዮጵያዊ ለመሥራት እጃችንን የምንዘረጋው፡፡እኛ ደርግ አይደለንም፡ ወያኔ አይደለንም፡ የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት አይደለንም፡ በስልጣን ላይ ያለን ወይም ሥልጣን ለመያዝ

የተቃረብን አይደለንም፡፡ እኛ እንደ ኦሮሞ ድርጅት ወንድሞቻችን ለፍትህ ለርትዕ ለዲሞክራሲ የምንታገል ብቻ ሳይሆን ከነሱ በላቀ ደረጃ ደግሞ የኢትዮጵያን አንድነት ለማስከበርና በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ሁሉ በሰላምና በብልጽግና ዴሞክራሲያዊ ስርአት ገንብተው የኢትዮጵያ አንድነት ተጠብቆ የምንኖርበት ሥርአት ለማምጣት የምንታገል ኢትዮጵያውያን ነን፡፡ ሌላው ዝባዝንኬ ጉንጭ አልፋ ክርክር ዞሮ ዞሮ ወቅን እንደሚሉት ነው፡፡

ጊዜው የኛን መጠናከርና መዳከም የሚተመንበት ነው ይህን ጥያቄ አዲስ (KIC) (ምክር ቤቱ) በቶሎ እልባት ካልሰጠው ችግሩ ወደር የለሽ ሆኖ ወደሌላም ይዛመታል፡፡ጊዜ ይሰጠው ወይም ለዶክተር ታዬ ጊዜ እንስጣቸው የሚባል ጥያቄ ሲቀርብ እንሰማለንና ይህን በሚመለከት አንድ ታሪካዊ ነጥብ መዘከር እንወዳለን፡፡

የጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሐብተወልድ ካቢኔ እንደፈረሰና ልጅ እንዳልካቸው አዲስ ካቢኔ አቋቁመው ሕዝቡ ተቃውሞውን ሲያስተጋባና ሲያስጨንቃቸው ያሉት አንድ ነገር ከህሊናችን የማይጠፋ እንደተረትም የሚነገርላቸው “ጊዜ ይሰጠን” አሉ የልጅ እንዳልካቸው መንግሥት ይባላል፡፡ በመሃሉ ደርግ ሁሉንም ነጥቆ 17 ዓመት ተሰቃየን (AFD) እንደተመሰረተ መሰረታዊ ችግር እንዳለበት ከየአቅጣጫው በድርጅት መልክ እነ ሕብረት፡ኢሕአፓ እንዲሁም ታዋቂ ምሁራንነ ግለሰቦች እንደነ አምባሳደር እምሩ፡እነ ዶክተር ታዬ ወ/ሠማያትና አያሌ የታረክ፡የፖለቲካ፡የሕግ ምሁራን የስምምነቱን ጎጂነት ዘርዝረው ባስረዱበት ወቅት ከ(AFD) ሰዎች ደጋፊዎችና መሪ ድርጅቶች አጥብቆ የተጠየቀው ነገር ቢኖር እንዲሰራ እናደርገዋለን <u>“ጊዜ ስጡን”</u> ነብር፡፡ ደጋፊዎችም ለተቃዋሚው ወገን <u>“ጊዜ ይሰጣቸው”</u> የሚል ተማጽኖ ነበር ያቀረቡት፡፡ ነገር ግን ማንም ለማንም ጊዜ ሰጪና ነፋጊ ሊሆን አይችልም፡፡የፖለቲካ ሕይወታችን አሁን አዲስ ነገር እየሞከርን አይደለም፡፡ ያለውን የተፈጸመውን ያጠፋውንና ያደማውን ካለፈው ተሞክሮ እያመሳከርን ፡ አምና፡ ታቻምና ያስቀመጥነው ቤት አሁንም በላዩ ላይ አራሙቻ በቅሎበት ወይም ኖራ ተቀብቶ ቢመጣ መሰረቱ ያልተለወጠው በዚያ ምሰሶ የቆመው ቤት ተለወጠ ብለን እንደ አዲስ ቤት አንዘፍንለትም፡፡

ጊዜ ወርቅ ነው (AFD) ከተቋቋመ አንድ ዓመት አለፈው በዚህም ጊዜ ተሠርቶ ያየነው አንድ ነገር ብቻ ነው፡፡ ኢትዮጵያዊው ድርጅት ሲዳከም ፡ ትቢያ ላይ ወድቀው ተረስተው የነበሩ አገር አፍራሽ ድርጅቶች ነፍስ ዘርተው በአውሮፓ ማሕበር ፡ በአፍሪካ ድርጅትና በተለያዩ ሐገሮች ታላቅ ድርጅት መስለው በ(AFD)ና በቅንጅት ጀርባ እራሳቸውን  ሲያጠናክሩና የኢትዮጵያን ሕዝብና አንድነት ሲያደሙ፡ ዓላማቸውንና ፕሮግራማቸውን ሲያጠናክሩ ነው የባጁት፡፡

ባለፈው አንድ ዓመት ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ልጆች የኢትዮጵያ አንድነት ፡ ህልውና ጭምር በ(AFD) እጅ በአካልም በህሊናም ሕዝባችንን ሲያደማ ከርሟል ፡፡ አሁንም ይደማል፡፡በሐገር መበተን ጉዳይ ተከሳሹና ተወቃሹ ወያኔ ብቻ አይደለም (OLF፣ ONLF) እንዲሁም መሰሎቻቸው ጭምር ናቸው፡፡ እየደማን ከወያኔ ጋር አብረን አንደራደርም፡ እየተጎሸምንና ካራ እየተሳለልን ከ (OLF) ጋር አብሮ መስራት አብሮ መብላት የሚባል ስንክሳር ከጨዋታ ውጪ ነው፡፡ ጥያቄው ከውሃ በጠራ መልክ በጣም ግልጽ በሆነበት ሰዓት ከመምህራን ማሕበር መሪነት ወደ ፖለቲካ ድርጅት መሪነት ስለተሸጋገሩ የጥያቄውን ባህሪ አይቀይረውምና የተጠናን የተተቸውን ጥያቄ ጊዜ አያስጠይቅም፡፡ የጊዜ ጥያቄ የሚነሳበት ወቅት አይደለም፡፡ Time for action! Adios AFD...Avanti Popolos.

ከላይ እንደተነተነው ፕሮግራማቸውን ለማስቀየር መንፈሳዊ ችሎታ አለው ብለን ማመን አለብን፡፡ ምኞት አንድ ነገር ነው፡ ተግባር ግን ይለያል፡፡ ቅንጅት መንፈስ ነው ፡ ቅንጅት ፍቅር ነው ፡ ሌላም ሌላም ሲባል ተከርሟል፡፡ከፖለቲካው አንፃር ከዚያ ተምኔት ወጣ እንበልና መንፈሳዊነቱን ለፕሮፓጋንዳው ክፍል ትተን በተጨባጭ የገጠመን ችግር ከመንፈስና ከፍቅር ርቆ እርስ በእርስ እያጋጨን ነው፡፡ የተመዘገቡ የቅንጅት አመራር አባትም መንፈሱን ወይም ፍቅሩን አላሳዩምና የምናየውን ተጨባጭ የፖለቲካ ሁኔታ ማጤንና ጊዜ ሳንሰጠው መልክ መያዝ አለበት፡፡

AFD እንደገና ሊታደስ ፡ ሊታረም የሚችል አይመስለንም፡ የከረረ ነውና፡፡ ከሆነ ዘንዳ ሙሉ በሙሉ ተፍቆ እንደገና ከኢትዮጵያዊነት የበላይነት አንፃር መመሥረት እንዳለበት ለድርድር የምናቀርበው አይደለም፡፡ ይህን ደግመን ደጋግመን የምናስረግጠውና እንኳን (KIC) ሸንጎው/ኮሚቴው ቀርቶ እስር ቤት ያሉት የቅንጅት አመራሮች ሙሉ በሙሉ በ(AFD) እንስማማለን ቢሉ ያለምንም ማወላወል የምንቃወማቸው መሆኑን ዶክተር ታዬም ሆኑ (Council)ሉ ካሁኑ አትኩረው ቢያዩት ድንቅ ነው እንላለን፡፡ በዚህም አኳያ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ይህን ጥያቄ ያለማወላወል ማንሳትና መወያየት ይጠቅማል፡፡

ዶክተር ታዬ በታጋይነታቸውና በቆራጥነታቸው እስከ ዛሬ ባሳዩት ተጋድሎ የምንኮራባቸው ቢሆንም ለሁሉም ኢትዮጵያዊነት ጥያቄ መልስ አላቸው ብለን አናምንም እንደሰው መጠን ስህተት ይሰራሉ ብንልም እንደበሳልነታቸው ደግሞ ቶሎ ስህተታቸውን አይተው ያርማሉ ብለን ለመገመት በቂ ምክንያት አለን፡፡

ቅንጅትን በመቀላቀላቸው እሰዬ ስንል በፖለቲካው መስመር ያላቸውን ልዩነት በተጨባጭ (AFD)ን እንደ ትልቅ ጥያቄ አንስተው የቅንጅት አመራር ለመውሰድ ላለመውሰድ ቅድመ ሁኔታ መሆን ነበረበት እንላለን፡፡ ሆኖም ከሆነ በምናየው አዝማሚያ (AFD) ተቀብለው ነው የተቀላቀሉት ለማለት ሙሉ በሙሉ ባንደፍርም አዝማሚያው ያን ይመስላል፡፡

ባጭሩ ይህን የተብላላና ያለቀለትን በአረጀ ጥያቄ ዶክተር ታዬ ከቀሰቀሱት ዘንዳ ለሕዝብ ያላቸውን ራእይ እንደገና ከቅንጅት መሪነት አኳያ ማብራራትና ማስረዳት ጊዜ የምንሰጠው ጥያቄ ወገባችንን ያጎበጠውና ጆሮአችንን ያደነቆረው ስለሆነ እንደተለመደው ጊዜ የለኝም፡ ስብሰባ ላይ ነኝ፡ የሚል መልስ በመስጠት ገለፃ እንደማይነፍጉን ተስፋ አለን፡፡

ስለ፡(AFD) በምናነሳበት ወቅት የ(AFD) አቀንቃኞች ከወያኔ መንግስት ጋር ሊኖራቸው የሚፈልጉትን ቅርርብና ግንኙነት ሳንጠቅስ ማለፍ አይቻለንም፡፡

(AFD) በመሰረቱ ጥሪውና አንደኛው ትኩረቱ የወያኔን መንግሥት አብሮ ማሳተፍና ማቅረብ ነው፡፡ ይህን ሀሳብ አጥብቀን የምንቃወምበትን ምክንያት በወቅቱ ብናሰማም አሁንም ለ(AFD) አቀንቃኞች የምናስታውሰው ነገር ቢኖር ለዶክተር ታዬ ጭምር፡፡

1. የወያኔ ጠባይና ባህሪይ ጠንቅቆ አለማወቅና የፖለቲካ ትንታኔ ብስለት ጉድለት ኢትዮጵያዊ ነን በምንለው በኩል መኖሩ አሁንም በሕገ መንግሥቱ ዓንቀጽ 39 ብቻ ሳይሆን ወያኔ ይህንን ዓንቀጽ ለመጠበቅ አጥብቆ መከላከሉ ብቻ ሳይሆን የወሮበላና ሕዝባዊ/ኢትዮጵያዊ ያልሆነ መንግሥት መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል፡፡
2. የቅንጅትን አመራር 8 ጥያቄ አቅርበው ለዚያ እንኳ ትህትና የተሞላበት መልስ ያልሰጠና ይባስ ብሎ በእስር እያማቀቃቸው እያለ የእነሱ መፈታት እንኳን ቅድመ ሁኔታ ሳይሆን አብሮ ለመስራት መደራደሪያ ሰነድ ይዞ መቅረብ ከ(AFD) አቋም የእኩልነት ጥያቄ ሳይሆን የእርቅ ሰነድ ወደ ወያኔ ለመሄድ የተዘጋጀ ሤራ ነው እንላለን፡፡

ሌላም ሌላም መሰረታዊ ስህተቶችና በኋላው ተንኮል ያዘለ ለመሆኑ ያደባባይ ሚስጢር ነው፡፡ የሻቢያ መንግሥት የዚህ ስብስብ መሥራችና አራማጅ መሆኑን ልንክድ አንችልም ለዚህም ዶክተር ታዬ በየተጋበዙበት ቦታ ሁሉ ስለ (AFD)ና ሻቢያ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሰጡት ቃለ መጠይቆች ከያሉበት መፈለግና ማጣቀስ ይቻላል፡፡

ስለ (AFD) አባላት (AFD)ን ከመሰረቱና ስለውበቱ ስለአቅሙ የተነበዩልንን ሳይሆን ያየነው ከቅንጅት የውጭው ወኪል ነን ባይ በስተቀር ሻቢያም፡ ኦነግም ሌሎችም በደቡብ ኢትዮጵያና በኦጋዴ አልፎም ከሱማሌው የኮርት መንግሥት ጋር ሆነው በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እያደረሱ ያለው ጥቃትና ወገንተኛነት ሕዝብን ከሕዝብ ማጋጨት ብቻ ሳይሆን ኢሰብዓዊ የሆኑ እርምጃዎች እየወሰዱ እንደሆነ ዛሬም ዶክተር ታዬ (AFD)ን ማጠናከር በሚሉበት ሰዓት የተንኮል ሥራቸውን አላቆሙም፡፡ (KIL)ም ሆነ የሻለቃው ቡድን የአሁኑ (KIC) ይህ የ(AFD) አባላት ተግባር አላወገዘም ተዉ ብሎ እንኳን አለመናቸውም፡፡

ስለዚህ ዶክተር ታዬን የምናሳስበው ቢሆን የነዚህን ጥያቄዎች ስፋትና ጥልቀት አስከፊ መዘዛቸውን ወደኋላ መለስ ብለው በመገምገም ካውንስሉ ወደ ኢትዮጵያዊነት ተግባሩ እንዲያተኩር ማድረግ የሚጠበቅባቸው ተግባር ነው እንላለን፡፡ምናልባት እኛ ያልታየን ነገሮች ካሉ በግልጽ ለሚደግፋቸው ሳይሆን ለሚቃወሟቸው ሥራዬ ብለው ማስረዳትና አሳምነውም ክርስዎ ጋር እንዲሰለፉ ማድረግ ከመሪነትም ከኢትዮጵያዊነትም አንፃር ሀላፊነትም ግዴታም ነው እንላለን፡፡

ሀሳቦች ሲቀርቡ ከዚህ መጣ ከዚያ ፈለቀ ሳይሉ ሁላችንንም በአንድነት አቅፈው በእኩልነት አይተው የጭንቀታችን ተካፋይ በመሆን ለመፍትሄው ድልድይ እንጂ ተጨማሪ እንቅፋት ይሆናሉ ብለን አናምንም፡፡

ከምንተስኖት ሲራክ

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!